PANORAMA # XXVIII

## የትዝብት አድማስ

ሰኔ 2000

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## በጋራ ሀገር በጋራ ለመኖር

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት፥ ተከፍቶም ይሁን ተደስቶ፥ ሠላምም አግኝቶ፥ ሠላምም አጥቶ፥ በውጭ ጥቃትም ጊዜ ይሁን፥ በውስጥ የጭቆና አገዛዝም አብሮ የኖረ ነው። ከጥንቱ ከጧቱ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመኖሩ ማዕከላዊ ነጥቡ የጋራ ሀገሩ ነበረች። አሁንም ነች። በጋራ ሀገሩ ደግሞ በጋራ ኖሯል። በዚህ መሠረታዊ ዕምነቱ ይመስለናል ዛሬ፥ ለፖለቲካ ድርጅቶች በመላ፥ እንደ ፖለቲካ ድርጅትነታችሁ፥ መስማማት ካልቻላችሁ፤ ሌላው ቢቀር፥ እባካችሁ በጋራ ሀገራችሁ በጋራ አብራችሁ የምትኖሩበትን ዘዴ ፈልጋችሁ፥በጋራ ለመኖር ተስማሙ እያለ የሚመክራቸው። እናንት ተሰማምታችሁ በጋራ መስራት ካልቻላችሁ፥ ለዘመናት አብሮ ተባብሮ የኖረውን ሕዝብ አትከፋፍሉት ይላቸዋል፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ። በጋራ ሀገራችሁ በጋራ ልትኖሩባት ስትችሉ፥ በጋራ ለመኖር የሚያስችላችሁን ሁኔታ አታበላሹት እየተባሉ ናቸው። ባጭሩ፥ በፖለቲካችሁ የጋራ ተግባር ለመፈፀም ካልቻላችሁ፥ ሀገሪቱ የሁላችሁም የጋራችሁ ነችና፥ በጋራ በሰላም እንኑርባት ብላችሁ ወስኑ። ሌላው ቢቀር ይህን ብቻ እንኳን ማድረግ ከቻላችሁ፥ ለሀገራችሁና ለሕዝባችሁ ታላቅ ተግባር እንዳከናወናችሁ ይቆጠርላችኋል እያላቸው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የፖሊቲካ ድርጅቶችን በመማፀን ላይ የሚገኘው፥ ኅብረት ለመፍጠር ባትችሉም እንኳ፥ በጋራ ሀገራችሁ በጋራ መኖር ይገባችኋል ብሏቸዋል። ሀገሪቷ ከአምባ ገነኖች ተላቀቀችም አልተላቀቀች፥ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች፥ በጋራ ተስማምተው በጋራ ሀገራቸው በጋራ የሚኖሩበትን ሁኔታ እያስተካከሉ መሄድ የግድ ማለቱን በግድ መረዳት አለባቸው። ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ካልተረዱ ደግሞ የሚያስከትለውን ሁለንተናዊ ችግር መገንዘብ የሚያዳግት ሊሆን አይችልም።

የጋራ ስምምነት ተገኝቶ፥ ጠንካራ የተቃዋሚ ጎራ መፍጠር ቀርቶ፥ ዛሬ፥ አዝማሚያው ሁሉ የሚያመራው፥ በጋራ ልንኖርባት የምንችለውን ሀገር በጋራ ማስኖር እንዳትችል ሊያደርጓት እየጣሩ ናቸው የአንዳንድ ድርጅት መሪዎች። እንዲያው ምንም ምን ምክንያት ይምጣ፥ ከእንግዲህ ወዲያ፥

በኢትዮጵያ አንድ ወይም ሁለት የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ሌሎቹን ብዙኃን ድርጅቶች፤ አጥላልቶም ይሁን፥ አግልሎ፥ አዳክሞም ይሁን አጥፍቶና አክስሞ ፥እነርሱ ብቻ ሥልጣን ላይ በመውጣት፥ ዘላቂ ሠላም ይሰፍናል ማለት ዘበት ነው። ይህን የማይገነዘብ የፖለቲካ መሪ ነኝ ባይም ይሁን ሌላው ዜጋ፥ እራሱን መመርመር ይኖርበታል። ለጋራ ጉዳይ የጋራ ባለቤትና የጋራ ኃላፊነት ከመፍጠር የበለጠ ሌላ ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣ ዘዴ አይኖርም። ይህንን መሠረታዊ ቁም ነገር እንደ ሌለ በመቁጠር፥ የግልና የቡድንን ምኞትና ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ሲባል የሚደረገው ግብዝነት ለሀገር ቀርቶ፥ ለግልም እንደማይጠቅም ማነኛቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች አፅንዖት በመስጠት ሊረዱት ይገባል። አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችም ይሁኑ ሌሎች ግለሰቦች በመገናኛ ብዙኃንም ይሁን በየሕዝባዊ ስብሰባዎች የሚሰጡት አስተያየትም ሆነ ንግግር፥ ሊያስከትል የሚችለውን ሁለንተናዊ አስተጋብዖ መገመትና ማመዛዘን ይጠበቅባቸዋል። ከሁሉ አስቀድሞ፥ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ የሚገባው፥ በሕዝብ አንድነትና ዘለቄታ ጥቅም ዙሪያ ሊካተቱ በሚችሉ ሁኔታዎች ላይ ሊሆን ይገባል። ይህን ሳይገነዘቡ ቀርተው፥ በጥላቻም ይሁን በዘፈቀደ የሚሰጡት አስተያየትና ቃለ-ምልልስ ሁሉ፥ ሕዝብን አስደንጋጭ ከመሆኑ አልፎ ተርፎ፥ ሌሎቹን ድርጅቶች ከስጋት ላይ ሊጥላቸውና ሊያስቆጣቸውም እንደሚችል ሊታወቅ ይገባል። ያም ስለተባለ ደግሞ፥ የአስበርጋጊ ታክቲክ መጠቀም ያዋጣናል የሚሉ ግለሰቦችና የድርጅት መሪዎች በያዙት ከገፉበት፥ የሚበረግግላቸው ማንም እንደሌለ ሊያውቁት ይገባል። የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ሊያድር ይችል እንደሁ እንጅ ሌላ ውጤት አይኖረውም። የሚያዋጣው ግን ተከባብሮና ተግባብቶ አብሮ መኖሩ ብቻ ይመስለናል። በቅርቡ አንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪ ነው የተባለሠ ግለሰብ ከአንድ የመገናኛ ብዙኃን ድርጅት ጋር ባደረገው ቃለ-ምልልስ፥ አንዳንድ ድርጅቶችን መጥፋት አለባቸው ብሏል። ፥ (ቃሉን የተጠቀሙት ኢሊሚኔት የሚለውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው።) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸውን ለማስመስከር ያደረጉትን ጥረት ብናደንቅም፥ በለመደ ደርጋዊና ወያኔያዊ አነጋገር እናጠፋቸዋለን የሚል ድፍረት በማግኘታቸው እንገረማለን። በአፍ ወንበዴዎች እስከማለት የሚያስችላቸውን ድፍረት በማግኘታቸው አድማጮቻቸውን ሁሉ እንዳስገረመና፥ እንዲያውም እንዳስቆጣና እንዳሳዘነ አያሌ የፖሊቲካ ታዘቢዎች ተናግረዋል። የዚህ ዓይነቱ ንግግር ታዲያ ምናልባት ተናጋሪዎቹ ተሳክቶላቸው ሥልጣን ቢይዙ፥ በወንበዴነት በፈረጇቸው ድርጅቶች ላይ፥ ምን ዓይነት እርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ መገመት አይከብድም ብለው የትዝብት አስተያየታቸውን የሚሰነዝሩ ታዛቢዎች በርካታ እየሆኑ መጥተዋል። ይህም የሚያመለክተው፥ መጭው የኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ምን ዓይነት መልክና ይዘት ሊኖረው እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም። ምናልባት የወያኔ መሪዎች፥ የተቃዋሚ ድርጅቶችን፥ ወንበዴዎች ማለታቸው አያስገርም ይሆናል፤ የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት ተቃውመን ቆመናል ከሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ይህን አስገራሚና ከፋፋይ የውንጀላ ቃል ሲጠቀሙ መስማት ግን ምን ዓይነት ትርጉም ሊሰጠው እንደሚቻል ግራ ያጋባል። ይህ መሠረታዊ ጭብጡን የሳተ፥ የኢትዮያን ሕዝብ የወቅቱን አንገብጋቢ ጥያቄና ፍላጎት የተፃረረ፥

በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ሊኖር የሚችለውን የአንድነትና የትብብር መንፈስ የሚበርዝና በጠቅላላውም የኢትዮጵያን የወደፊት ብሩኅ ተስፋ የሚያጨልም አስተያየትና ድርጊት መቆም አለበት። ይህ ካልሆነ፥ ተጠቃሚው ወያኔ ብቻ እንደሆነ/እንደሚሆንም ማንም ይስተዋል ማለት አይቻልም። አውቆ ከሚያጠፋው በስተቀር።

እንዲያው ዕውነቱን እንነጋገር ከተባለ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለመጭው የወያኔ ምርጫም ይሁን ማን እንደሚያሸነፍ ደንታ የለውም። ለምን ቢባል፤ ውጤቱን አስቀድሞ ስለሚያውቀው ነው። የወያኔን ሥልጣን ለማጠናከር በሚደረገው የምርጫ ሽርጉድ ምክንያት፥ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሲነታረኩ መስማትና ማየት ግን በእጅጉ ያሳዝነዋል። እንደገና በዚህም ክስተት የሚጠቀመው አሁንም ያው ወያኔ ብቻ ነው። በበኩላችን ዛሬም ይሁን ነገ ቅድሚያ የምንሰጠው ለሀገራችን ብሔራዊ ጥቅምና ለሕዝባችን ዘለቄታ አንድነትና ሀገራዊ ልዕልና ነው። ይህን መሠረታዊ ዕምነት ከሚጋሩልን ሁሉ ጋር እንተባበራለን። በጋራ ሀገራችንም፥ በጋራ ሊያኖረን በሚያስችለን በማንኛውም ጉዳይ ሁሉ ዕውን እንዲሆን ተግተን እንሠራለን። ለዚህ ዓላማና ግብ ዕንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉትን ሁሉ እንቃወማለን። የቅድሚያ ምኞታችንም፥ ሀገራችንን ከወደቀችበት አዘቅት ማዳን ነው። ሕዝባችን በብሄረሰብና በኃይማኖት እንዳይከፋፈል የተቻለንን ሁሉ የመከላከል ተግባር መፈፀም ነው። ለእነዚህ መሠረታዊና ዓበይት ሀገራዊ ጉዳዮች ትኩረት የምንሰጠውም፥ ለአርምሞ ግንዛቤ እንዲሆን ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ ምክንያት ስለአለን ብቻ ነው። ሀገርና ሕዝብ ከሌሉ፤ ማለትም፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከሕዝቦቿ ጋር ከሌሉ፥ ሌላው ሁሉ ትርፍ መሆኑን በፅኑ ስለአመንበት ነው። ይህ ዕምነታችን ደግሞ የትግላችን መነሻና መድረሻ የታሪካችን አልፋና ዖሜጋ፥ ብሎም፥ የመሥዋዕታችን ራዕይና ግብ በመሆኑ ነው። ከማንኛውም በላይና በበለጠ ደረጃ፥ የኢትዮጵያና ሕዝቧ መኖር ለእኛ ልዩ ትርጉምና ህላዌ አለው። ኢትዮጵያ ሀገራችንንም ሆነ ሕዝባችንን እንዳማራጭ አናያቸውም። እንደ ዓይነታ እንጅ። ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ የሚሉትን ከፋፋዮች ሁሉ አምርረን ስንታገላቸው የኖርነውም በዚህ ፅኑ ዕምነታችን ነው። ወደፊትም ቢሆን ይህንን የፀና ዕምነታችንን ሊያስለውጠን የሚችል ምድራዊ ኃይል ይኖራል ብለን አናምንም።

ይህ ከሆነ ዘንዳ፥ ከሰባ ሚሊዮን በላይ ዜጎች ያላት ሀገራችን የሁላችንም የጋራ ቤታችን መሆኗን አምነን መቀበል አለብን። ዜጎችን በዘርም ሆነ በክልል፥ እንዲሁም ፖለቲካ ድርጅቶችን ደግሞ፥ በዕምነታቸውና በታሪካቸው፥ በይዘታቸውና በዓላማቸው እየፈረጁ መከፋፈል አይጠቅምም እንላለን። በተለያዩ ሀገራት፥የተለያዩ ፕሮግራሞች፥ ዓላማና ግብ ያላቸው ብዙኃን የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ ሀገራቸው በጋራ ተስማምተው እንደሚኖሩ እናውቃለን። አንዱ ሌላውን ለማጥፋት የሚያደርገውን ስልትና ድርጊት ግን አላየንም። ምክንያቱም፥ ይህን ክስተት ቢከተሉ፥ አጥፊና ጠፊ የሚሆኑ መሆናቸውን አበክረው ስለሚረዱ ይህንን አይሞክሩትም። በነፃ ተወዳድረው ግን አንዱ አሸናፊ ሲሆን ሌላው ችንፈቱን አምኖ በመቀበል በሰላም ከመኖር

የበለጠ ብልጎነት እንደሌለም ይረዳሉ:: ለዚህ ሁሉ መሠረቱ ግን የዴሞክራሲ ሥርዓት መስፈን ነው:: ዛሬ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የጠማት ሀገር ነች:: በመሆኑም የአምባገነን ሥርዓት ነቃቅሎ ለመጣል ያለው ምርጫ ያው አንድ ብቻ ነው:: ይኸውም የተቃዋሚ ጎራ ተጠናክሮ አብሮና ተባብሮ መቆም ነው:: ይህ ጉዳይ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ እስኪሰለቸው ድረስ ተደጋግሞ ተደጋግሞ የተነገረ በመሆኑ፥ ብዙ ማለት አይቻልም:: በዴሞክራሲ ሥርዓት መተዳደር የታደሉ ሀገሮች፥ የፖለቲካ ድርጅቶች ተስማምተው በጋራ ሀገራቸው በጋራ ለመኖር ከቻሉ፤ በእኛይቱ ኢትዮጵያም ቢሆን፥ ይህ ሁኔታ የማይኖርበት ምክንያት ይኖራል ብለን አናምንም:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፥ አንድ መሠረታዊ ሀቅ መኖሩን ለማስመር እንፈልጋለን:: ይኸውም፥ ተወደደም ተጠላ፥ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ገፅታና ነባራዊ ሁኔታ በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ግዴታቸው መሆኑን፥ ለፖሊቲካ ሥልጣን እንታገላለን የሚሉ ድርጅቶች ሁሉ ሊያውቁት የሚገባቸው የፖለቲካ ሀሁ መሆኑን ነው:: ኢትዮጵያ ሀገራችን የአያሌ ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን አምኖ ካልተቀበሉ፥ እንዲያው ከመጀመሪያው ትልቅ መሠረታዊ የአመለካከት ችግር አለ ማለት ነው:: የተለያዩ ብሔረሰቦች መኖር ደግሞ ጥንካሬ እንጅ፥ ድክመት እንዳልሆነ፥ ብልፅግና እንጅ ድኅነት እንዳልሆነ፥ መታደል እንጅ አለመታደል እንዳልሆነ፥ ጌጥና ኩራት እንጅ ኃፍረት እንዳልሆነ፥ ሁሉም አውቆ የጋራ ሀገራችን የጋራ መኖሪያችን መሆኗን አምኖ መቀበል ከተቻለ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት የሚደረገው ከንቱ ሙከራ ዋጋ ቢስነቱ ታውቆ የሚወገድ ይመስለናል:: ያለፈው እርስ በእርስ መጠፋፋትና ሀገርን የመጉዳት ክስተት መቆም አለበት:: የጦርነትን ምንንት ከራሱ ከባለቤቱ፥ ከባለጉዳዩ፥ ከጦርነቱ ተሳታፊ ከወታደሩ የበለጠ የሚያውቅና የሚጠላ ያለ አይመስለንም:: በሞተ -ከዳ የሚመጣውና የሚሾመው በሚገባ አያውቀውም:: የፖለቲካ ትግልን መራራነትና መስዋዕትንም በሚገባ ሊያውቀው የሚችለው ለረዥም ዓመታት በትግሉ የተሳተፈውና አይከፍሉ መሥዋዕት የከፈለው ብቻ ነው:: ለዚህም ይመስለናል፡ በጋራ ሀገራችን በጋራ ለመኖር ስንል ብዙ መከራን ስንቀበል የቆየነው::

በፖለቲካው የበሰሉ ክፍሎች በድርጅቶች መሀል የፕሮግራም ልዩነት መኖሩ ፀጋ መሆኑ ይገባቸዋል:: በሀገር ህልውና ጉዳይ፤ ሀገርን ከጥፋት በማዳኑ ላይ ስምምነት እስካለ ድረስም በዝርዝር ጉዳዮች ላይ የሚከሰቱ የተለያዩ አቋሞች የሚያጋድሉ አይደሉም:: ነፃ ሀገርን፤ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ማረጋገጥ ከቻልን ሕዝብ በነፃ ምርጫ የሚበጀውን ይመርጣልና ነው:: ከወዲሁ ከእኔም ሌላ ድርጅት ለአፈር ማለት፤ በራስ ፕሮግራምና ሥራ መሰረት ድጋፍን ከማግኘት ፈንታ፥ በሌላ ድርጅት ላይ አፀያፊ ዘመቻ በመክፈት ተከታይ ለማግኘት መሞከሩ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል:: ወያኔ በሀሳብና በአቅዋም የተቃረነውን ድርጅት ሁሉ ጠላት ብሎ ለማውደም ሲጥር ታይቷል፤ዛሬም የተለየ አቋም የለውም:: ይህ ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲነት መሆኑ በገሀድ የታየ ነው:: ለሀገራችን የሚበጃትም አንድ ወይም ሁለት ድርጅት ብቻ ነው ብሎ መበየንና መደንገግ አይቻልም:: የድርጅቶችን ህልውና ወሳኝ ሕዝብ ብቻ ነው:: የሚደግፋቸውን አቅፎ በማጠናከርና የማይፈልጋቸውን ድጋፍ ነስቶ

በማጫጫት የሕዝብ ውሳኔና መብት ነው:: ስለዚህም ዛሬ አንዳንዶች ከአንድ ወይም ሁለት ድርጅት ውጪ ሌላ መኖር የለበትም፤ የብሄረሰብ ድርጅቶችም መኖር የለባቸውም የሚሉት ጠቃሚ ሳይሆን ጎጂና መብትን ረጋጭ ነው:: አዳዲስ ድርጅቶችም በተግባራችን ፍረዱን ማለት አለባቸው እንጂ፥ በተመሰረቱ ማዕግስት በነባር ድርጅቶች ላይ የጥላቻ ዘመቻ መክፈት የለባቸውም:: ዘመቻ ከተከፈተ የተጠቃው ደግሞ ሊከላከል መመለሱ የግድ ይሆናል:: ግርግሩም ለወያኔ ሰርጎገቦች አንዱን ወይ ሌላውን ደጋፊ መስለው ረብሻን እንዲፈጥሩ/ እንዲያባብሱ በር ይክፈትላቸዋል:: በበኩላችን ሀ ብሎ ትግል ሲጀመር በህብረ ብሄራዊ ደረጃ ለኢትዮጵያ ብለን የተደራጀን ብንሆንም የሌሎችን መደራጀት ግን ተቃውመን አናውቅም--ሁሉም ለኢትዮጵያና ለዴሞክራሲ እስከታገለ ድረስ::

በአሁኑ ወቅት በተቃዋሚ ድርጅቶች መሀል የተካረረ ልዩነት መኖሩ ይታያል:: ይህ መቀጠል የለበትም-መወገድ ይኖርበታል:: ድርጅቶች ቅራኔዎችን አርግበው፤ ነገር አባባሾችን አስወግደው፤የወያኔ ሰርጎገቦችን አሳፍረውና መንጥረው ለጋራ ሀገራቸው በጋራ መቆም አለባቸው:: አንዱ የሌላው ጠላት አይደለምና:: ዛሬ በድርጅቶች መሀል ቅራኔ በማባባሱ ተልዕኮ ላይ ተሰማርተው የሚገኙት በተለይም በባዕድ ሀገር ያሉ ግለሰቦችና በየስብሰባውና በድረ ገፅ መርዛቸውን የሚረጩት ናቸው:: የድርጅቶች ደጋፊ መስለው ቅራኔ ያባብሳሉ:: በወንጀል እንጠየቃላን ብለው የፈሩና በከህዲነት ሕዝብ ለፍርድ ያቀርበናል ብለው የሰጉትም ቢሆኑ አጥፊ ዘመቻቸውን ከፍተዋል:: ሰላም ከመጣ፥ ፍትኀ-ርትዕ ከሰፈነ፥ ጉዳችን ፈላ ባይ ናቸው:: ድርጅቶች እርስ በርስ ከመነታረክ ይልቅ የጋራ ሀገራችንን ለማዳን ትዕግስቱም፤ ሆደሰፊነቱም፤ ብርታቱም ፅናቱም ይኖራቸው ዘንድ እንመኝላቸዋለን:: በፖለቲካ አመለካከትና በትግል ስልት ባንስማማም ለጋራ ሀገራችን ብቻ ስንል ልዩነቶቻችን አቻችለን በጋራ ሀገራችን በሰላም ልንኖር የምንችልበትን ሁኔታ መፍጠርና ማጠንከር አለበን:: እኛ ዛረ ቅድሚያ የሰጠነው ከማነኛውም በላይ ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ጥረት ላይ ነው:: በአሁኑ ወቅት ሀገራችንን ከአምባገነኖችና ከዘረኞች መንጋጋ ማላቀቅ የቅድሚያ አጀንዳቸን አድርገነዋል:: ለእኛ የሀገራችን መኖር አልፋና ኦሜጋችን ነው:: የሀገራችንን መኖር በአስተማማኝ ደረጃ ካረጋገጥን ሌላው ወቅቱን እየጠበቀ የሚመጣ ይሆናል:: ቀጣዩና ዓይነተኛው ጉዳይ፥ በሕዝብ ወሳኝነት አምኖና ተቀብሎ በጋራ ሀገራችን በጋራ በሰላም መኖር ብቻ ነው::

ለከፋፋዮች አንመች:: ለሰርጎገቦች አንመች:: ማን ይሻል ማን ጥያቄን ሕዝብ በነፃ ምርጫ እንዲወስን ትተንለት የመለስን አገዛዝ በማስወገድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ እንታገል::